THE FREEDOM FUND

# ኢትዮጵያውያን ሴቶች በመካከለኛው ምስራቅ በቤት ውስጥ ሥራ ላይ እንዲሰማሩ የሥራ እና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎችና የደላሎች ሚና

## ፍትኃዊ የሥራ ሥምሪት የሠራተኞች የምልመላ ሞዴሎች ላይ ከመነሻችን ጥናት የተገኙ ዉጤቶች ማጠቃለያ

መስከረም 2022 ዓ.ም

ለንደን ስኩል አፍ ኃይጂን እና ትሮፒካል ሜዲስን



LONDON SCHOOL of HYGIENE &TROPICAL MEDICINE

POPULATION COUNCIL
Ideas. Evidence. Impact.

DEPARTMENT OF STATE · UNITED STATES OF AMERICA

# ማጠቃለያ

በርካታ ኢትዮጵያውያን ሴቶች የቤት ዉስጥ ስራ ፍለጋ ወደ መካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ይሰደዳሉ፡፡ ይህ ማህበራዊ አዝማሚያ፣ ኢትዮጵያውያን ቤተሰቦች እና ማህበረሰቦች የተንሰራፋውን ድህነት ለመጋፈጥ የሚጠቀሙበት ዋነኛ የመተዳደርያ ስልት ነዉ (Kuschminder, Andersson and Seigel, 2018; Zewdu, 2018)፡፡ ከስደተኞች ቁጥር ብዛት የተነሳ፣ ከስደት ጋር የተያያTh ጥናቶች በጣም ሰፊ ናቸው፡፡ ነገር ግን በአብዛኛው በ"ገፊ" እና በ"ሳቢ" ምክንያቶች ላይ በማተኮር ስደት ሊያስከትሏቸዉ የሚችለዉን ለምሳሌ የጉልበት ብዝበዛ፣ በህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር፣ የስደተኞች አካላዊ፣ አእምሮአዊ እና ጤናማ የወሲብ ፍላጎት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ስጋቶች ላይ ያተኩራሉ (Avalew and Minaye, 2017; Gezie et al., 2019; Habtamu, Minaye and Zeleke, 2017; Reda, 2018)፡፡ ይህ ጥናት ሴቶች የስደት ጉዞአቸውን እንዴት እንደሚያቅዱ፣ ለተለያዩ ዉሳኔዎች በማን እንደሚተማመኑ፣ ለኢኮኖሚ እና ለተግባራዊ እርዳታ በማን እንደሚተማመኑ ከሚዳስሱት ጥናቶች አንዱ ነዉ፡፡ እንዲሁም፣ ጥናቱ መደበኛ መልማዮች እና ተራ ደላሎች በሴት ስደተኞች ላይ ያላቸዉን ሚና ይዳስሳል፤ ይህም ሴቶቹ ከኢትዮጵያ ወደ መዳረሻ ሀገራት ጉዞ በሚያደርጉበት ጊዜ፣ ከደረሱ በኋላ እና ወደ ኢትዮጵያ መመለስ በሚፈልጉበት ጊዜ ሊኖራቸዉ የሚችለዉን ሚና ዳስሷል፡፡

ይህ ሪፖርት የ"**መነሻችን**" ገላጭ ጥናት ከመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፎች የተገኙትን ግኝቶች በአንድ ላይ አካቷል፡፡ የ"መነሻችን" ገላጭ ጥናት በመካከለኛው ምስራቅ አገራት በተለይም እንደ ሳዑዲ አረቢያ፣ የተባበሩት አረብ ኢምሬትስ (UAE)፣ ሊባኖስ እና ኩዌት ባሉ መዳረሻዎች የቤት ውስጥ ስራን ለመስራት ከኢትዮጵያ ለሚሄዱት ሴቶች የምልመላ እና የማመቻቸት/ማስተባበር አሰራሮችን ቃኝቷል፡፡ የምዕራፍ አንድ ጥናት (በአዲስ አበባበ ዉስጥ ለ69-ሰዎች ቃለ-መጠይቅ በማድረግ የተጠና ጥናት) (Busza, Shewamene and Zimmerman, 2021) መሰረት፣ የሁለተኛዉ ምዕራፍ ጥናት ደግሞ በዋናነት የስደት ምልመላ ተለዋዋጭነት፣ እቅድ እና አመቻቾች ላይ ያተኮረ ሲሆን ይህም በሂደቱ ውስጥ ከአዲስ አበባ ዉጪ በቅርበት ከተሳተፉት ሰዎች እይታ አንጻር ነው። በባህር ዳር ከተማ እና በሃዲያ ዞን ከ87 በላይ የሚሆኑ በስደት ላይ የሚሰሩ የሀገር-በቀል ባለድርሻ አካላት፣ መደበኛ ያልሆኑ የስደት አስተባባሪዎች፣ ከመካከለኛው ምስራቅ የስደት ተመላሾች፣ እጩ ስደተኞች፣ በመካከለኛው ምስራቅ ከሚገኙ የቤት ሰራተኞች ወላጆች ጋር ጥልቅ ቃለ-መጠይቅ ተደርጓል፡፡ እነዚህ ጥናቱ የተካሄደባቸዉ አከባቢዎች ከዋና ከተማው (ከአዲስ አበባ) ርቀው የሚገኙ ነገር ግን ብዙ ስደተኞች የሚሰደዱበት እንዲሁም "ላኪ" ማህበረሰቦች ተብለው በምዕራፍ-1 ጥናት የተለዩ ናቸዉ፡፡

መንግስት እና ሌሎች ተቋማት መረጃን ወደ ላኪ ማህበረሰብ ለማድረስ ባደረጉት ጥረት ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በስደት ሊደርሱ ስለሚችሉ አደጋዎች ግንዛቤ ጨምሯል። በቃለ-መጠይቁ መረጃ መሰረት፣ ይህ ጥናት የተካሄደበት አከባቢ የሚኖሩ ማህበረሰቦች "በህጋዊ መንገድ መሰደድ" ላይ ጥሩ ግንዛቤ ቢኖራቸዉም ይህንን ግን መከተል አልቻሉም፡፡ ምክንያቱም፣ በአከባቢያቸዉ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ፈቃድ ያላቸው ግለሰቦች ባለመኖራቸው እና ወደ አዲስ አበባ መጓዝ እና አገልግሎቱን ማግኘት የሚፈልጉ የማህበረሰብ ክፍሎች ቀላል አይደለም፡፡ ስለዚህ፣ በጣም የተለመደው አካሄድ በግል የሚያውቋቸውን በመተማመን ሲሆን፣ ብዙውን ጊዜ በጥቆማ ወዳገኙት አስተባባሪ የመሄድ አዝማምያ አላቸዉ፡፡ ለመሰደድ በመወሰን እና ወደ አዲሱ የስራ ቦታቸዉ በመድረስ መካከል ያለዉን ግዜ ለማሳጠር ሲባል በስደተኞች የሚያዉቁትን የመጀመሪያ አመቻችን/አስተባባሪን ሊመርጡ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪ፣ መመዝገቢያ ማስረጃዎችን የሚያቀርቡ መካከለኛ አስተባባሪዎች መኖራቸዉን የተጠየቁት እጩ ስደተኞች፣ የቤተሰብ አባላት እና ተመላሾች ለዚህ ምላሽ ለመስጠት ፍቃደኛ አልሆኑም። ምክንያት ይህ ጥናት የተደረገበት አከባቢ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች በአዉሮፕላን የሚደረግ ጉዞ ሁሉ የህጋዊ ስደት ማሳያ ነው ብለዉ ስለሚያምኑ ነው።

የስደት አመቻቾች/አስተባባሪዎች፣ ተሰዳጆችን ለህገ-ወጥ ዝዉዉር ሊያጋልጡአቸዉ የሚችሉትን የተለያዩ ልምምዶች እንደሚጠቀሙባቸው በኢትዮጵያ ዉስጥ የተሰሩ ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡ የስደት አመቻቾች ስደትን እንደ ስራ/ቢዝነስ ይቆጥሩታል፤ የሚከፈላቸዉም ሊሰደዱ የሚችሉ ሰዎችን ሲያስገኙ ነዉ፡፡ ጥቅማ ጥቅማቸዉን ለማግኘት ሲባል፣ የስደት አስተባባሪዎች የስደት ጥቅም እና ስጋቶች/አደጋዎች ዙሪያ ሊሰደዱ ለተዘጋጁ ሴቶች የተጋነነ ወይም አሳሳች መረጃዎችን ይሰጣሉ፡፡ በተጨማሪም፣ ሀሰተኛ ሰነዶችን ማዘጋጀት እና መደበኛ ፍተሻዎችን ማሳለፍ የስደት አመቻቾች ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ነዉ፡፡ በስደተኛ ጉዞ ውስጥ የሚሳተፉ ሰዎች ቁጥር ከፍተኛ ሲሆን ግኑኝነታቸዉም የሚደረገዉ ከትናንሽ ደላላዎች እስከ በርካታ ግለሰቦችን በሚያሳትፍ በተዘረጋ "ሰንሰለት" በኩል ነዉ፡፡ ብዙዎቹ የስደት አስተባባሪዎች በ"ሰንሰለት" ውስጥ ያላቸው ሚና ከተጠናቀቀ በኋላ ለስደተኞች ደህንነት ተጠያቂዎች ነን ብለዉ አያስቡም። እነዚህ መካከለኛ የስደት አስተባባሪዎች (የማህበረሰብ አባላትን በአዲስ አበባ በሚገኙ መልማዮች ጋር የሚያገናኙ)፣ ከህግ ማዕቀፎች ውጪ ከሚንቀሳቀሱ መልማዮች እና በህግ ማዕቀፍ ዉስጥ የሚንቀሳቀሱትን መልማዮች መለየት አይችሉም። በዚህ ምክንያት ለተፈጠረው ብዝበዛ ተጠያቂ ግለሰቦችን በ"ሰንሰለት" ውስጥ ለመያዝ የሚደረገውን ጥረት ያወሳስበዋል።

ስደትን በማመቻቸት ዉስጥ ሁሉም ፆታ የሚሳተፍ ቢሆንም አቀራረባቸዉ ግን ይለያያል፡፡ ምንም እንኳን ጥናቱ በትንሽ ናሙና ላይ የተመሰረተ ቢሆንም፣ ሴት አስተባባሪዎች ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር አደጋን የሚቀንሱ አንዳንድ አሰራሮችን እንደሚጠቀሙ ሪፖርት ተደርጓል፡፡ ሴት አስተባባሪዎች ስደትን ለማመቻቸት በግል የሚያውቋቸዉን የመጠቀም እድላቸው ሰፊ ሲሆን ይህም በረጅም "የምልመላ ሰንሰለት" ውስጥ ያለውን ተሳትፎ ይቀንሳል። ሴት አስተባባሪዎች ስደተኞችን እንደማያታልሉ በአፅንዖት በመግለፅ ትክክለኛ መረጃ እና ምክር እንደሚሰጧቸዉ ይናገራሉ፡፡ ከስደተኞች የሚገኘዉን ጥቅም አስመልክቶ፣ አንዲት ሴት የስደት አመቻች "ክፍያ ከስኬት በኋላ" በማለት ገልጻዋለች፤ ይህም ስደተኛዋ በሰላም መዳረሻዋ መድረስዋን እስክትገልጽ ድረስ የስደት አመቻቿዋ ክፍያ የታመኑ የማህበረሰብ መሪዎች ጋር ይቀመጣል፡፡ ክፍያዋም የሚከፈለዉ በዚህ መልኩ ብቻ ነዉ፡፡

የስደት አመቻቾቹ፣ በመዳረሻ አገሮች ውስጥ በስደተኛዋ ላይ ሊደርስ የሚችለዉን የህገ-ወጥ ዝዉዉር መቆጣጠር አይችሉም፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የስደት- አመቻቾችም ሆነ የውጭ ሀገር ስራ እና ሰራተኛ አገናኝ የኤጀሲዉ ኃላፊነት ስደተኛዋ ኢትዮጵያን ስትለቅ ያበቃል ብለዉ ያስባሉ፡፡ በተጨማሪም፣ ስደተኞቹ ላይ የሚደርሰው ሁሉ በአሰሪዎቻቸው እና በቤት ሰራተኞች አያያዝ ዙሪያ ባለው የአገሪቷ ደንቦች ኃላፊነት ነዉ ብለዉ ያስባሉ፡፡ በተጨማሪም ኢትዮጵያ ውስጥ ጥቂት ኤጀንሲዎች የራሳቸው የሆነ ሰራተኛ ውይም ወኪል በውጭ ሀገር ቀጥረዋል፡፡ ሆኖም፣ አብዛኞቹ የማህበረሰብ አካላት ተጽእኖ ሊያሳድሩ በማይችሉ እና ህጋዊ ብቃታቸውን በማያውቁት የሀገር ውስጥ መልማዮች ይተማመናሉ፡፡ በኢትዮጵያ ህግ መሰረት ሁሉም ህጋዊ ኤጀንሲዎች $100,000 (~500, 000 ብር) በመንግስት ቁጥጥር ስር ባለው አካውንት ማስያዝ አለባቸው፤ ይህም ኤጀንሲዎቹ ላስቀጠሯቸዉ ሰራተኞችን ለካሳ (ለምሳሌ ለጉዳት ካሳ፣ እንግልት ወይም ወደ ሃገር የመመለሻ ወጪዎች) የሚያግዝ ገንዘብ ነዉ፡፡ ነገር ግን፣ በአሁኑ ጊዜ የተጠያቂነት ባህል ያለ አይመስልም። ከቃለ-መጠይቁ ተሳታፊዎች መካከል ከአንዲት መጠይቅ መላሽ በስተቀር አንዳቸውም የይገባኛል ጥያቄዎችን እንዴት ማቅረብ እንደሚቻል የሚያውቁ አልነበሩም።

በውጭ አገር የቤት ዉስጥ ሥራ ላይ የተሰማሩ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ላይ የሚደርሰዉን የጉልበት ብዝበዛና ሕገ-ወጥ የስዎች ዝውውርን ለመቀነስ፤ የጥናቱ ግኝቶች ለኢትዮጵያ መንግስቲ፣ ለመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና በዉጪ አገር ለሚገኙ አሰሪና ሰራተኛ አገናኝ እንዱስትሪዎች፣ የሚከተለዉን ምክረ-ሀሳቦችን ሰጥተዋል።

## በኢትዮጵያ ላሉ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች

- ለቤት ዉስጥ ሰራተኛ በተለያዩ የመዳረሻ አገራት ውስጥ ስላሉት የስራ ሁኔታዎች እና ክፍያዎች ለእጩ ስደተኞች ትክክለኛ መረጃን መስጠት።
- ህጋዊ ስደት እና ህጋዊ ያልሆኑ የስደት ሂደቶች ላይ የእጩ ስደተኞች ግንዛቤን ማሳደግ።
- በመዳረሻ አገራት ላይ ትኩረት ያደረገ መደበኛ የሆነ እና ያልሆነ የድጋፍ ስልቶች ላይ ለሁሉም (በህጋዊ መንገድም ሆነ ህገወጥ ለሆኑ) እጩ ስደተኞች መረጃ መስጠት።

## በኢትዮጵያ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የመንግስት ሚኒስቴር መስሪያቤቶች

- በህጋዊ መንገድ መሰደድ ለሚፈልጉ ሁሉ በቅልጥፍና እና በቀላሉ የሚፈልጉትን ህጋዊ ሰነዶችን እንዲያገኙ ማድረግ፤
- በአካባቢ ማህበረሰብ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ታማኝ ደላሎች/ንዑሳን የኤጀንሲ ወኪሎች እና በተቋቋሙ መልማዮች መካከል ያለውን ግንኙነት ህጋዊ ማድረግ እና እዉቅና መስጠት፤
- ለህጋዊ እና አስተማማኝ ስደት ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር እንዲችሉ መልማዮችን በሕግ እና በፖሊሲ ግምገማ ውስጥ እንደ አዎንታዊ ማህበራዊ ወኪሎች ማሳተፍ፤
- በሁሉም የስደተኛ ጉዞ ዉስጥ የተሳተፉትን መልማዮችና በመዳረሻ አገራት የሚገኙ ባልደረባዎቻቸውን ተጠያቂ ለማድረግ ከመድረሻ ሀገር መንግስታት ጋር ግንኙነት ማድረግ፤
- ለቤት ዉስጥ ስራ ለሚሰማሩ ስደተኞች እና የዉጪ ሀገር አሰሪዎች ያለውን የስራ ሁኔታ ለማስፋፋት፣ ከመዳረሻ ሀገራት ጋር አዳዲስ እና ያሉትን የሁለትዮሽ የስራ ስምምነቶች ለማሻሻል ቀጣይነት ያለዉን ውይይት ማድረግ፤
- ለስደተኞች ከለላ የሚሰጡ ህጎችን እንዲያወጡ እና አጋዥ ዘዴዎችን እንዲዘይዱና ተግባራዊ እንድያደርጉ ከመዳረሻ ሀገራት መንግስታት ጋር ዉይይት ማድረግ፤

## ለውጭ ሀገር  ሥራ ሥምሪት የሠራተኞች ምልመላ ኢንዱስትሪዎች

- የተለያዩ አጋዥ ስልቶችን በመጠቀም የአገሪቷ ደንቦች መተግበሩን እና ለመልማዮች አዳዲስ ህጎች እና ሂደቶች ላይ ትምህርት መስጠቱን ማረጋገጥ። ይህ ሲሆን፣ መልማዮች ለእጩ ስደተኛ የቤት ዉስጥ ሰራተኞች ምክር ይሰጣሉ።
- በዉጪ አገር ለሚገኙ የኢትዮጵያዉያን የግል ስራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች የአለም አቀፉ ሥራ ድርጅት የሥነ-ምግባር ደንቦችን እንዲያሟሉ ድጋፍ መስጠት።
- በሕግ ማዕቀፎች ዉስጥ እንዲሰሩ እና የስደተኞችን ጥቅም እንዲያረጋግጡ፣ የቀጣሪዎችን እና የኤጀንሲዎችን አቅም ማጎልበት።

## በውጭ ሀገር ለሚገኙ ለኢትዮጵያ ሚሲዮን

- በሕግ ማዕቀፎች ዉስጥ እንዲሰሩ እና የስደተኞችን ጥቅም እንዲያረጋግጡ፣ የቀጣሪዎችን እና የኤጀንሲዎችን አቅም ማጎልበት።
- በዉጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ለስራ ጉዳይ በውጭ የሚመደቡትን በእውቀት እና በስልጠና የተደገፉ በማድረግ እና ለዲፕሎማቲክ ሰራተኞች የሚመደበዉን በጀት በኢትዮጵያ የውጭ ሀገር ስራ ስምሪት አዋጅ 923/2016 እና ማሻሻያ አዋጅ 1246/2021 መሰረት ማድረግ።
- የመዳረሻ አገራት ኤጀንሲዎች/ወኪሎች ክትትል እና ሪፖርትን በማሻሻል፣ የቤት ዉስጥ ስራ ላይ የተሰማሩ ስደተኞችን የመጠበቅ ግዴታቸውን እየተወጡ መሆናቸውን ማረጋገጥ።
- በመዳረሻ አገራት የሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች የሚጠቀሙትን ወቅታዊ አሰራር ላይ ምርምር እና ግምገማዎችን ማካሄድ።

## በመዳረሻ አገራት ለሚገኙ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች

- የስደት ሁኔታቸው ምንም ይሁን ምን ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ተደራሽ የሚሆን የአደጋ ጊዜ ፈንድ መመደብ።
- በመዳረሻ አገራት የቤት ዉስጥ ሥራ ላይ የተሰማሩ ስደተኞችን የሚያገናኝ አማራጭ ዘዴዎችን/መንገዶችን መደገፍ።
- ስልታዊ ሙግትን እንደ መሳርያ በመጠቀም የቤት ዉስጥ ስራ ላይ የተሰማሩ ስደተኞች ላይ የሚደርሰውን በደል፣ በአሰሪዎቻቸዉ የሚደርስባቸውን ጥቃቶች እና በወኪሎች የሚፈፀምባቸዉን ድርጊቶችን ማጉላት።

ፍሪደም ፈንድ ዘመናዊ ባርነትን ለማጥፋት በአለም አቀፍ ደረጃ የሚደረገዉን እንቅስቃሴ የሚመራ ድርጅት ነዉ፡፡ ዘመናዊ ባርነት በጣም የተስፋፋባቸው አገሮችን እና ዘርፎችን በመለየት በጣም ውጤታማ የሆኑት ግንባር-ቀደም ጥረቶችን በመለየት ድጋፍ እናደርጋለን።

ባለ ራዕይ ከሆኑ ባለሀብቶች፣ መንግስታት፣ ፀረ-ባርነት ድርጅቶች እና ለብዝበዛ ከተጋለጡት አካላት ጋር በመተባበር፣ ባርነት እንዲቀጥል እና እንዲስፋፋ የሚያደርጉትን ስርዓቶችን እንታገላለን፡ ፡ ከእነኚህ ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመስራት፣ ተጋላጭ ህዝቦችን እንጠብቃለን፣ በባርነት የተያዙትን ነፃ እናወጣለን ወደ ቤተሰቦቻቸዉ እና ማህበረሰቦቻቸዉ እንመልሳቸዋለን፡፡ እንዲሁም ለወንጀሉ ተጠያቂ የሚሆኑትን ለህግ እንዲቀርቡ እናደርጋለን፡፡

**The Freedom Fund (US)**
315 Flatbush Avenue
#406
Brooklyn, NY 11217
USA
+1 929 224 2448

**The Freedom Fund (Ethiopia)**
Mayswi Building 7th Floor
Ethio-China Ave
Addis Ababa
Ethiopia
+251 (0) 976 - 80 0506

**The Freedom Fund (UK)**
Lighterman House
30 Wharfdale Road
London, N1 9RY
UK
+44 20 3777 2200

**London School of Hygiene & Tropical Medicine**
Keppel Street
London WC1E 7HT
United Kingdom
+44 207 636 8636

**Population Council**
One Dag Hammarskjold Plaza
New York, NY 10017
United States
+1 212 339 0500

www.freedomfund.org
info@freedomfund.org
@Freedom_Fund

The Freedom Fund is a United States 501(c)(3) public charity (EIN number 30-0805768).
The Freedom Fund UK is a company limited by guarantee registered in England and Wales (company number 08926428) and a registered UK charity (registration number 1158838).